1/ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 8460 የካቲት 18 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27682 ኅዳር 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው ናቸው ብለናል፡፡ ስለዚህ ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡

2/ ተጠሪዋ በጋብቻው ወቅት ከአቶ አሰፋ መለሰ ደሞዝ ለቤቱ ዕዳ ለባንክ የተከፈለው ገንዘብ እና የመድን ድርጅት እዳውን ለመጨረስ የከፈለው የሕይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ ተደምሮ የድምሩ አንድ አራተኛ /25%/ ይከፈላቸው፡፡ አከራካሪው በወዳ 19 ቀበሌ 55 የሚገኘው ቁጥሩ 223 የሆነው ቤት ግን የአቶ አሠፋ መለሰ የግል ሐብት ነው ብለን ወስነናል፡፡

3/ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 29899 ጥቅምት 17 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ 279

4/ ከዚህ ችሎት ጥር 29 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

5/ ግራ ቀኙ የዚህን ፍ/ቤት ወጪ በየራሣቸው ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

280 የሰበር መ/ቁ. 23389

ሐምሌ 10 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
አሰግድ ጋሻው
ተሻገር ገ/ሥላሴ
አብዱራሂም አህመድ
ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አክ/ማኅበር - ጠበቃ ኃይሉ አስምር ቀርቧል፡፡

ተጠሪ፡- እነ ባህሩ አብርሃም /12 ሰዎች/ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ይህ ጉዳይ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመ/ቁ 08449 ላይ በታህሣሥ 27 ቀን 1997 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ብይን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ 37119 ላይ

በሕዳር 27 ቀን 1998 ለዋለው ችሎት ብይኑን በማፅናቱ አመልካች የካቲት 15 ቀን 1998 ዓ.ም. ባቀረበው ማመልከቻ በስር ፍ/ቤቶች የተፈፀመው የሕግ ስህተት እንዲታረም በመጠየቁ ነው፡፡

የሰበር ችሎቱም መዝገቡን መርምሮ የማኅበሩ አባላት በአስተዳዳሪዎች ላይ ክስ ሊመሰርቱ የሚችሉበት የሕግ አግባብ ምን እንደሚመስል ለማጣራት ሲል ቅሬታው ለተጠሪዎች ደርሶ ታህሣሥ 19 ቀን 1999 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ቀርበው በጠበቃቸው አማካይነት የቃል ክርክር አድርገዋል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም መዝገቡን መርምሯል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ክስ ሲመሰርቱ ተጠሪዎች የአክስዮን ማኀበር አስተዳዳሪዎች ሆነው ከደንብ ውጪ በአክስዮን ማኀበሩ ከተሰራው ሕንፃ ውስጥ የግንባር ሱቆችን በተደረገው ግልጽ ያልሆነ ስብሰባ ያሳለፉት ውሣኔና የወሰዱት አስተዳደራዊ ውሣኔ ከደንቡ ውጩ እንዲታገድና እንዲፈርስ የሚል አቤቱታ አቅርበው ለመጀመሪያ ት ተጠሪዎች በሰጡት መልስ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ተጠሪዎችን እንደማይመለከትና እንደማያስከስሳቸው፣ ያስከስሳቸዋል ቢባልም እንኳ በን/ህ/ቁጥር 365/1/ መሠረት በተጠሪዎች ላይ ክስ ለመመሥረት የሚቻለው ማኀበሩ እንጂ አመልካቾች ሊሆኑ እንደማይችሉ በመቃወማቸው ፍ/ቤቱም ክርክራቸውን በመስማት አመልካቾች በንግድ ሕግ አንቀጽ 365 ሥር የተመለከተውን ቅድመ ሁኔታ ሳያሟሉ በተጠሪዎች ላይ ክስ መመሥረት አይችሉም በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

በዚህ ችሎትም የታየው መሠረታዊ ጉዳይ አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ በቀጥታ ክስ መመሥረት ይችላሉ ወይ የሚለው የሕግ ጥያቄ ነው፡፡ በንግድ ሕግ አንቀጽ 364 እስከ 367 በተደነገገው መሠረት የአክስዮን ማኀበር አስተዳዳሪዎች ሀላፊነት ለአክስዮን ማኀበሩ አበዳሪዎች፣ ለአክሲዮን ማኀበሩ ባለድርሻ አባላት ወይም ለሦስተኛ ወገን ሊሆን እንደሚችል ተመልክቷል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ላይ ተጠሪዎች የአመልካቾችን መብት በሚጎዳ መልኩ የሰሩ ስለሆነ ሃላፊነት አለባቸው፣ የሰሩትም ሥራ ሊፈርስ ይገባል



የሚል ክስ የቀረበባቸው መሆኑ በሥር ፍ/ቤት መዝገብ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ሆኖም የበታች ፍ/ቤት ክሱን ውድቅ ለማድረግ መሠረት ያደረገው የሕግ አንቀጽ የንግድ ሕጉ ቁጥር 365 ቅድመ ሁኔታዎች አልተሟሉም የሚል ነው፡፡ ሆኖም በዚህ አንቀጽ ድንጋጌ የተመለከተው ማኀበሩ አስተዳዳሪዎችን ለመክሰስ ሲፈልግ ሊያሟላ የሚገባውን ቅድመ ሁኔታዎች እንጂ የተወሰኑ የአክሲዮን ማኀበሩ ባለድርሻዎች የሚያቀርቡትን ክስ አያጠቃልልም፡፡

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው አስተዳዳሪዎች ላይ ክስ ለመመሥረት የሚችሉ ወገኖች ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች በንግድ ሕጉ ለየብቻ የተደነገገ ስለሆነ እነዚህን ለይቶ በአግባቡ ማየት የግድ ይሆናል፡፡ በዚሁ መሠረት አሁን በተያዘው ጉዳይ ላይ አመልካቾች የሚሉት በተጠሪዎች የተፈፀመው ተግባር መብታቸውን የሚጎዳ በመሆኑ አስተዳደሪዎችን /ተጠሪዎች/ በቀጥታ መክሰስ የበታች ፍ/ቤት አንቀጽ 365ን መሠረት አድ ሉ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡

እኛም ይህንን ሁኔታ ከላይ እንደተመለከተው የተጠያቂነት መሠረቱ ለየብቻ መታየት እንዳለበት የሕጉን ዓላማና መንፈስ መሠረት አድርገን አጽንተነዋል፡፡ በዚሁ መሠረት አመልካቾች የአክስዮን ባለድርሻ አባላት በመሆናቸው የአባልነት መብታቸውን በሚጎዳ መልኩ አስተዳዳሪዎች /የአሁን ተጠሪዎች/ መሥራታቸውን ማረጋገጥ ከቻሉ ቀጥታ መከሰስ እንደሚችሉ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 367 ይፈቅድላቸዋል፡፡

በመሆኑም አመልካቾች የሚጠበቅባቸው በተጠሪዎች ሥራ አመራርና የውሣኔ እርምጃ ተጎጂ መሆናቸውን በንግድ ሕጉ አንቀጽ 367 መሠረት ማረጋገጥ እንጂ የበታች ፍ/ቤት እንደተመለከተው በንግድ ሕግ አንቀጽ 365 የተመለከተውን ቅድመ ሁኔታ ማሟላት አይጠበቅባቸውም፡፡ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 365 የተወሰኑ የአክስዮን ማኀበሩ አባላት በአስተዳዳሪዎች ላይ የሚያቀርቡትን ክስ የሚመለከት ስላልሆነ የሥር ፍ/ቤት ተገቢ ያልሆነውን የሕግ አንቀጽ መሠረት አድርጎ የአመልካቾችን ክስ መዝጋቱ የሕግ ስህተት ነው ብለናል፡፡